# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 67 ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም


> እኛ የምንታገለዉ ከአሶሳ እስከ ጎዴ ከዛልአምበሳ እስከ ሞያሌ ባሉት የኢትዮጵያ ግዛቶች ዉስጥ ተወልዶ የሚያድገዉ የደሀ ገበሬ ልጅ የወደፊት ዕድሉ የሚወሰናዉ በጎሳዉና በዘሩ ሳይሆን በባህሪዩና በችሎታዉ ብቻ እንዲሆን ነዉ።
>
> አቶ **ኤፍሬም ማደቦ** ዴንቨር በግንቦት7 ስብሰባ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ

## የኦባማ አስተዳደር ዘረኛውን ወያኔን እያገለለ ያለበት ሁኔታ የወያኔን ሰፈር ከፍተኛ ድንጋጤ ኣስገብቶታል

ከአሜሪካ ጋር እየተበላሸ የመጣውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ሊያስተካክልልኝ ይችላል በሚል ጭንቀት፣ ወያኔ አዲስ አምባሳደር ለመሾም በዝግጅት ላይ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

በቡሽ አስተዳደር ዘመን በጠራራ ጸሃይ በህዝባችን ላይ ለፈጸማቸው የጭፍጨፋ ወንጀሎች ከአያሏ አገር አሜሪካ ሀይ አለመባሉን የመልካም አስተዳደር ሙገሳ አድርጎት የኖረው ወያኔ፣ በአዲሱ የኦባማ አስተዳደር አጅግ አንዳልተደሰተ የሚያመለክቱ በርካታ ተግባሮችን ሲፈጽም አንደነበረ ከነዚህም አንዱ የስቴትስ ዲፓርትመንት ያወጣዉን የሰብአዊ መብት አያይዝ ሪፖርት ለማጥላላት 90 ደቂቃ በፈጀ ቅንብር በኢትዮጵያ ቴለቪዝን የተላለፈው ስድብና ማንጓጠጥ ጉልህ ማስረጃ እንደሆነ ይታወቃል።

ገና ከተሾመ አጭር ጊዜ የሆነውና ወያኔን በአሜሪካን አገር አምሳደርነት ያገለገለው ዶክተር ሳሙኤል አሰፋ ከሀላፊነቱ እንዲነሳና የበለጠ ታማኝነት አለው የሚባለዉ የወያኔ ተላላኪ መመደቡ ያስፈለገበት ውሳኔ ከተስፋ መቁረጥ ስሜት የመነጨ ነው ተብሏል። አምባሳደሩ በታማኝነት አገዛዙን ለመከላከል አልቻለም የሚል ተደጋጋሚ ወቀሳ ይቀርብበት እንደነበር የግንቦት 7 የውጭ ጉዳይ መስሪያቤት ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ከላኩልን ወሬ ለማረጋገጥ ተችሎአል። የመለስ አገዛዝ ዶክተር ሳሙኤል አሰፋን በተለመደው አሰራሩ ተጠቅሞበት ይጣለው ወይንም ለሌላ ሹመት ይጩው የታወቀ ነገር የለም ተብሎአል።

ወያኔ በኦባማ አስተዳደር የደረሰበት መገለል ከባድ ግምት የሚሰጠው እና ትልቅ ፓለቲካዊ አንድምታ ያለው ነው ያሉት አንድ ያነጋገራናቸው ታዛቢ፣ አዲሱ አስተዳደር እንደተጠበቀው ሁሉ በጸረ-ሽብርተኛነት ስም ከወያኔ ጋር አለመስራቱ ያስመሰግነዋል ብለዋል። ኢትዮድያን የሚያክል የአፍሪካ ህብረት መስራች እና መቀመጫን ትተው ሉአላዊነታቱን እንኳን ማስከበር ያቃታትን የሱማሊያን ፕሬዝዳንት ሂላሪ ክሊንተን ማነጋገራቸው፣ መለስ ዜናዊ በኦቦማ የጋና ጉብኝት ላይ አለመጠራቱ የኦባማ አስተዳደር ከወያኔ ጋር ለመስራት ላለመፈለጉ ግልጽ አብነቶች ናቸው የሚሉት ምሁሩ፣ **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## በአለም የመጨረሻዋ ደሀ ሃገር ኢትዮጵያ የአሜሪካ ባለስልጣነትን ለማግባባት ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ለድለላ ስራ እንደምታወጣ አንድ ታዋቂ ድህረ ገጽ አጋለጠ

ፕሮ ፓብሊካ የተባለ አንድ ድህረ ገጹ የአሜሪካን ባለስልጣናትን ለመደለል፣ በእንግሊዝኛው አጠራር ሎቢይ ለማድረግ ከፍተኛ ገንዘብ ከከፈሉ አገሮች መካከል የአለም ደሀዋ አገር ኢትዮጵያ አንዷ መሆኑዋን ጠቅሷል።

ድህረ ገጹ አያይዞም ኢትዮጵያ ከፍተኛ ገንዘብ የምትከፍለው ዲኤል ኤ ፓይፐር ለተሰኘው የድለላ ተቋም ሲሆን፣ ለዚሁ ድርጅት ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እንደመደበችም አጋልጧል፡፡ የወያኔ አገዛዝ ከደሀው ጉሮሮ እየቀማና ከ10 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ተርቦ፣ ለአሜሪካ ባለስልጣናት መደለያ ማዋሉ፣ ወያኔ ለአገርና ለህዝብ የማያስብ አጥፊ ቡድን መሆኑን ያሳያል ሲሉ አስተያየት የሰጡን ኢትዮጵያውያን በቁጣ ተናግረዋል።

ይህ በ'እንዲህ አንዳለ ሰቆቃ እና ፍዳ አምራቹ የወያኔ አገዛዝ ማዳበሪያ ለገበሬዎች በመከልከሉ ምክንያት በርካታ ኢትዮድያዊያን እየሞቱ እንደሆነ የአሜሪካ ድምጽ ዘግባል። በአርሲ ዞን ኢዶላ ቦርቃ፤ በመሀል አሮሚያ ሎሚና በሻሸመኔ በወያኔ ሰራሹ ድርቅ በግፍ እንዲያልቁ የተፈረደባቸው የኦሮሞ ገበሬዎች ማዳበሪያም ሆነ ምርጥ ዘር እንዳይገዙ መከልከላቸውን በአለፈው ሳምንት በምሬት ለአሜሪካ ድምጽ ተናግረዋል። አንድ በኢዶላ ቦርቃ የሚኖሩ ገበሬ ከሰሞኑ ብቻ በቅርበት የሚያውቋቸው አራት ህጻናት በምግብ እጦት መሞታቸውን እና ጎረቤታቸው የነበሩ አዛውንትም በተመሳሳይ ሁኔታ መሞታቸውን ተናግረዋል።

በወያኔ ብልሹ እና ሃላቀር የኢኮኖሚ ፓሊሲ እንዲራብ እና ከሞት ጋር አሰቃቂውን ግብግብ እንዲያደርግ የተፈረደበት የኢትዮድያ አቋሙ እየተመዘነ የእርዳታ ምግብ እንደሚሰጠው የገፈቱ ቀማሾች ተናግረዋል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ወያኔ ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁንን ከእስር የለቀቀው በመጪው ምርጫ የወጣቶችን ድምጽ ለማግኘት አስቦ መሆኑን ታዋቂው ዘ ኢኮኖሚስት የተባለው መጽሄት ገለጸ

መጽሄቱ፣ በፖለቲካ ምክንያት ታስሮ እንደነበር በብዙዎች ዘንድ የሚታመነው ቴዲ አፍሮ ከእስር የተለቀቀው እስከመጨው ምርጫ ድረስ ፖለቲካዊ ዘፈኖችን እንዳይዘፍን ተደርጎ ሊሆን እንደሚችል ገልጾ፣ የአርቲስቱ መፈታት የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ሊ/ር የሆኑትን ወ/ት ብርቱካንን ጉዳይ ይበልጥ ወደ መድረክ እንደሚያመጣው ዘግቧል።

መጽሄቱ፣ በፖለቲካ ምክንያት ታስሮ እንደነበር በብዙዎች ዘንድ የሚታመነው ቴዲ አፍሮ ከእስር የተለቀቀው እስከመጨው ምርጫ ድረስ ፖለቲካዊ ዘፈኖችን እንዳይዘፍን ተደርጎ ሊሆን እንደሚችል ገልጾ፣ የአርቲስቱ መፈታት የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ሊ/ር የሆኑትን ወ/ት ብርቱካንን ጉዳይ ይበልጥ ወደ መድረክ እንደሚያመጣው ዘግቧል። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ፋሽሽቱ መለስ ዜናዊ ቀዶ ጥገና ተደርጎለት ተመለሰ

የበርካታ ወጣት ኢትዮጵያውያን ደም በማፍሰስ የሚታወቀው ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በቤልጂየም አገር በብራስልስ ከተማ በሚገኝ አንድ ሆስፒታል የቀዶ ህክምና ተደርጎለት ባለፈው ሳምንት ሃሙስ ወደ አገሩ እንደተመለሰ ምንጮቻችን ገልጸዋል።

የበሽታውን ምንነትና የተደረገለትን ህክምና አይነት ለማጣራት ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ተኝቶ ይታከምበት ወደ ነበረበት ሆስፒታል ተልኮ የነበረ የግንቦት 7 ዘጋቢ፣ የግለሰቡ ለህክማና ከአገር መውጣት ዜና በሬዲዮናችን መተላለፉ ከተሰማ በሁዋላ በተፈጠረባቸው ከፍተኛ የመረበሽ ስጋት ይመስላል ተጨማሪ የጥበቃ ሰራተኞች ከኢትዮጵያ ከመጡ አጃቢዎቹ ጋር በመሆን በአካባቢው **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ አገዛዝ በመማረር የሚጠፉና ዜግነታቸውን የሚቀይሩ አትሌቶች ቁጥር እየተበራከቱ ናቸው

የዘረኛው መለስ አገዛዝ በዘር ላይ ተመርኩዞ የሚያራምደው ፖሊሲ በስፖርት ቤተሰቡ ውስጥ እንኳን ሳይቀር ዘልቆ በመግባቱ፣ በርካታ አትሌቶች አገራቸውን ጥለው በመሰደድና ዜግነታቸውንም በመቀየር ላይ መሆናቸው ታውቆአል::

ከነዚህም አብዛኞቹ አትሌቶች የባህሬንና የሌሎች አገሮችን ዜግነት በመውሰድ ላይ እንደሚገኙ የታወቀ ሲሆን፣ በፌደሬሽን ውስጥ ያለው ዘረኝነት፣ ሙስናና ስነምግባር የጎደለው አሰራር አትሌቶቹ ዜግነታቸውን እንዲቀይሩ እንዳደረገቻው በምክንያትነት ይጠቀሳሉ። በተለይ በሴት አትሌቶቹ ላይ የሚደርሰው ጾታዊ በደል ከፍተኛ መሆኑን የሚናገሩት ምንጮቻችን፣ ዜግነታቸውን የሚቀይሩትና የሚሰደዱት ሴቶች ሆነዋል ብለዋል።

ሰሞኑን በበርሊን የአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ጨዋታዎች የታየው ውጤት ለዚህ ማስረጃ ነው የሚሉት ምንጮቻችን፣ ስፖርተኞቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያስመዘግቡት ውጤት እየተዳከመ መምጣቱንም ተናግረዋል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ኢትዮጵያ እውቀቱ በሌላቸውና ጤና በጎደላቸው ሰዎች የምትተዳደር አገር ናት ስትል አሜሪካዊት ተማሪ ተናገረች

በኦሮሚያ ክልል በሀረማያ አካባቢ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ለማስተማር በፈቃደኝነት ዘምተው ከነበሩ አሜሪካኖች መካከል ሮኒ ሊናኒ የተባለች አስተማሪ ይፋ ባደረገችው ጽሁፍ ላይ እንደገለጸችው፣ የወያኔ ገዢዎች እጅግ ሁዋላ ቀሮችና ራሳቸውን ከፍ አድርገው የሚያዩ በሽተኞች ናቸው ስትል ተሳልቃባቸዋለች።

ተማሪዋ የወያኔ ሹማምንት በእርሷና በባልደረቦቿዋ ላይ ያደረሱትን ግፍ አንድ ባንድ ዘርዝራ "ይህ ግፍ የደረሰብንም የኦሮሞ ልጆችን ለማስተማር ወደ ክልሉ በመሄዳችን ነው" ስትል አስገራሚ የሆነ መልስ ሰጥታለች። **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## በኢትዮጵያ ሰላማዊ ፖለቲካ ትግል እንደማይቻል የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና አንድነት ፓርቲ አስታወቁ

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ባለፈው ሳምንት በናዝሬት ከተማ በአንድነት አመራሮች ላይ የደረሰውን መዋከብ አስመልክተው ባወጡት መግለጫ እንደጠቀሱት፣ በአዳማ ከተማ በወያኔ ሹመኞች የተወሰደው አሳፋሪ አርምጃ በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ ስራ ለመስራት መንቀሳቀስ በማይቻልበት ደረጃ ላይ መደረሱን ያረጋግጣል ነው ብለዋል ::

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በበኩሉ ባለፈው ነሀሴ 11 ቀን ባውጣው ባለሁለት ገጽ መግለጫው በኢትድያ የፓለቲካ ምህዳሩ ጨርሶ መዳፈኑን በተግባር አርጋግጬአለሁ ሲል ገልጾአል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

# ርእሰ አንቀጽ



## የአዳማውም ክስተት የወያኔ አጠቃላይ ፓሊሲ አካል ነው፤ ምላሹን የምንሰጠውም ራሱ ወያኔን በማስወገድ ነው

ከግንቦት 1997 ወዲህ “ምርጫ” የሚለው ቃል ብቻውን ወያኔን ያሸብረዋል። እንኳንስ የምር የውሸት ተፎካካሪ እንኳን በሌለበት ሁኔታም ቢሆን በምርጫ ወቅት ወያኔ መደናበሩ አይቀርም። ይህንን ደግሞ በአለፈው ዓመት ”የአካባቢና የማሟያ ምርጫ” በተሰኘው ከሶስት ሚሊዮን በላይ ሰዎች በተመረጡበት አስቂኝ የምርጫ ተውኔት በግልፅ የታየ ሐቅ ነዉ። በዚያ ምርጫ ከተወዳዳሪዎቹ ዘጠና አምስት በመቶ ያህሉ ወያኔዎችና ምስለኔዎቻቸው ነበሩ። ያም ሆኖ ግን ወያኔ «ምረጡኝ» እያለ ሰውን ማንገላታቱ፤ ከአስር ሺህ ተወዳዳሪዎች ውስጥ አንድ የወያኔ ተቃዋሚ ከተገኘ እሱኑ ማዋከብ ሥራዬ ብሎ ይዞት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።

በግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት የነፃ ተቋማት መኖር ከምርጫ በላይ አስፈላጊ ነገር ነው። ነፃ ተቋማት ካሉ አንድ ምርጫ ቢበላሽ በሌላ ምርጫ ይስተካከላል፤ ተቋማቱ ከሌሉ ግን ምርጫ የለም። ከምርጫ 97 የተማረነው ትልቁ ትምህርትም የነፃ የተቋማት ሚና ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ነው። ከምርጫ 97 ወዲህ ደግሞ የወያኔ ተቋማት ይበልጥ አፋኝና በሚያሳፍር መልኩ ከቀድሞው የባሰ ዘረኛ ሆነዋል። በዚህም ምክንያት የ2002 ዓ.ም አገራዊ ምርጫ እየተቃረበ ሲመጣ የወያኔ መደናበር የሚፈጥራቸው አሳዛኝ ክስተቶችን መታዘባችን አልቀረም። ነሐሴ 10 ቀን በአዳማ ከተማ በአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ መሪዎች፣ የክብር እንግዶቹና ደጋፊዎቹ ላይ የደረሰው እንግልት ከእነዚህ ክስተቶች ከመጀመሪያዎቹ አንዱ ነው፤ ወደፊት ከዚህም የባሱ አሳዛኝ ክስተቶ እንደሚኖሩ መጠበቅ ብልህነት ነው።

ጉዳዩ በአጭሩ የሚከተለው ነበር፡፡ ነሐሴ 10 ቀን 2001 ዓ.ም አንድነት ፓርቲ በአዳማ ከተማ የጠራው ስብሳባ ሲጀመር የወያኔ ምስለኔ የሆነው የኦህዲድ ካድሬዎች «ነፍጠኛ በምድራችን ላይ አይንቀሳቀስም፣ ለነፍጠኞች አሳልፎ የሸጠንን ነጋሶን ማየት አንፈልግም፣ ሴት ልጅ በመድረክ ላይ ወጥታ ንግግር ማድረጓ የኦሮሞን ባህልና ህዝብ መናቅ ነው፣ ነፍጠኞች በአማርኛ ቋንቋ አንሰማችሁም! ስብሰባው በሸማግሌ ምርቃት መከፈት ነበረበት! ...» ሌላም ሊጻፉ የማይገባቸው አስነዋሪ ቃላትን በመናገር በተቀነባበረ ጩኸትና ፉጨት ስብሰባው እንዲቋረጥ አደረጉ። የስብሰባው አዘጋጆችና እንግዶች ከአዳራሹ የወጡት የስድብ ናዳ እየወረደባቸውና በመገፍተር ጭምር ነበር።

ይህ የአዳማው ክስተት፡-

1. ወያኔ ዘረኝነትን ለምስለኔዎቹም በማስተማር እኩይ ሥራው በተወሰነ መጠን ውጤት እያስመዘገበና ራሱን የመሰሉ ዘረኞች በየቦታው እያመረተ ስለሆነ የኢትዮጵያ አገራችን ሕልውና አደጋ ላይ መሆኑ፤
2. ጉልህ የሆነ ስጋት ባይኖርበትም እንኳን ወያኔ በለስላሳ ተቃዋሚዎቹ ላይ ሳይቀር ምን ያህል ነውረኛ ተግባር የመፈጸም አቅል እንዳለውና ከዚህም በላይ ከመፈጸም የማይመለስ እርኩስ መሆኑ፤
3. ሕብረተሰቡን በእለት ተእለት ተግባር ማገልገል ያለባቸው የፓሊስና የቀበሌ ጥበቃ አባላት ሳይቀሩ ምን ያህል ወገንተኛ መሆናቸውና ወያኔ ፊታቸውን ያጠቆረባቸው ሰዎች በማጅራት መቺዎች ቢመቱ እንኳን ደርሶ የሚያስጥላቸው የሌለ መሆኑን፤ እና
4. ባጠቃላይ በአገሪቷ ውስጥ ህግ የሚባል ነገር ፈጽሞ መጥፋቱን ያመለክታል።

የአዳማው ክስተት የተፈፀመው የ2002 የቅድመ-ምርጫ ዘመቻ ገና ተፋፍሞ ሳይጀመር መሆኑ ዘመቻው ሞቅ ካለ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ፍንጭ የሚሰጥ ነው። ከአዳማ በፊትም በመቀሌ አረና ትግራይ፤ በባህርዳር ደግሞ አንድነት በጠራቸው ስብሰባዎች ላይ ተመሳሳይ ፍንጮች ተስተውለው ነበር። ስለሆነም የአዳማው የተናጠል ክስተት አይደልም። የአዳማው ክስተት የወያኔ ኢትዮጵያን የመግዣ ትልቁ ፓሊሲ አካል እንጂ በተለይ ከአዳማ ከተማ ወይም ከኦሮሚያ ክልል ወይም ከኦሮሞ ማኅበረሰብ ጋር የሚያያዝ አይደለም። ነገ በጋምቤላ፣ በአሶሳ፣ በጅጅጋ፣ በሐረር፣ በድሬዳዋ፣ በአሳይታ፣ በደሴ፣ በጎንደር .... በማናቸውም የኢትዮጵያ የክልል ከተሞች የተቃማዊ ፓርቲዎች ስብሰባ ከጠሩ ተመሳሳይ ወይም ከዚህ የባሱ ነገሮች መፈፀማቸው አይቀርም። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ አዲስ አበባ ውስጥም ይፈፀማል ይህ የምናውቀው የወያኔ ባህሪይ ነው።

ግንቦት 7 ነፃ ተቋማት ሳይኖሩ ምርጫ ውስጥ መግባት ለእንደዚህ ዓይነት ስብእናን ለሚያዋርዱ፤ የሕዝብን ሞራልና ስነልቦና ለሚጎዱና በአገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የምናደርገውን ጥረት ለሚያወሳስቡ ጥቃቶች እንደሚያጋልጥ ከመግለጽም አልፎ መፍትሄውንም አመላክቷል።

ይህንን በአገርና በህዝብ ላይ የሚፈፀም ወንጀል ለመከላከል መፍትሄው የወያኔን ጨዋታ አለመጫወት ነው ብሏል። ዳኛ እንደሌለ፤ ተፎካካሪው ጠበኛና ነውረኛ እንደሆነ እየታወቀ ጨዋታ ውስጥ ከተገባ በኋላ «ተገፋሁ፣ ተረገጥኩ» ተብሎ ለማን አቤት ይባላል? ለጊዜው ጨዋታውን አለመጫወት መብት ስለሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ በትኩረት እንዲያጤኑት እንመክራለን። ወያኔ ይህንን መብት ሊገፍ እንደሚችልና በግድ «ተወዳድራችሁ ተሸነፉ» ሊል እንደሚችል በጊዜ ማወቅ ይበጃል እንላለን። ዋነኛው መልእክታችን ግን በምርጫው ተሳትፈን ለውጥ እናመጣለን ብለው ለሚያስቡት ፓርቲዎች ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።

በአዳማ የተፈፀመው ድርጊት እጅግ አሳስቦናል። ስጋታችን ከኢትዮጵያ ህልውና ጋር እንጂ ከምርጫ 2002 ጋር የተያያዘ አይደለም። የወያኔ «ከፋፍለህ ግዛው» ፓሊሲ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የራሳቸው ያደረጉ ግለሰቦችንና ቡድኖችን በየቦታው ተራጅተዋል። በዚህ ከቀጠለ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሁሉም «የኔ ከተማ የኔ ብቻ!!» እንዲል ይደረጋል። ይህ ደግሞ የወያኔ ህልም የሆነው የኢትዮጵያን መጥፋት እውን ያደርጋል፤ በምትኳም የሚመጡ ሌሎች አገሮች አይኖሩም። ይልቁንስ እርስ በርሳችን ስንጣላ ወያኔ ያለተቀናቃኝ አገራችንንም እኛንንም ይበላል። ይህንን አደጋ ነው ዛሬ ማስቆም ያለብን። የወያኔ መጫወቻዎች መሆናችን ሊያሳፍረንና ሊያንገበግበን ይገባል እንላለን። በምንም ሁኔታ ይፈፀም ምርጫ 2002 ለዚህ መፍትሄ አይሰጠንም። ዘላቂ መፍትሄው ወያኔን አስወግደን በነጻ ምርጫ በሚመጣ መንግሥት አማካይነት ችግሮቻችንን በሰላማዊ መንገድ የምንፈታበት ሥርዓት ማቆምና ለዚህ የሚረዱ ተቋማትን መፍጠር ነው። ይህ ነው የግንቦት 7 ተልእኮ።

ወያኔ በድንበር፣ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በፓለቲካ እንዲያው ባገኘው ሰበብ ሁሉ ሊያፋጀን ይሻል። ይህ መላዋን ኢትዮጵያ የመቆጣጠሪያ ፓሊሲው አካል ነው። የአዳማውም ክስተት የወያኔ አጠቃላይ ፓሊሲ አካል ነው፤ ምላሹን የምንሰጠውም ራሱን ወያኔን በማስወገድ ነው።

## የኦባማ አስተዳደር ዘረኛውን ወያኔን . . . ከገጽ 1 የዞረ

የኦባማ አስተዳደር በወያኔ አገዛዝ መሰላቸቱንና ሌሎች አማራጭ መንገዶችን በማየት ላይ መሆኑን አመልክተዋል።

የወያኔ ሰፈር በአሜሪካ በደረሰበት መገለል ከባድ ሽብርና ድንጋጤው ውስጥ መግባቱን የሚደርሱን መረጃዎች ያሳያሉ። ከፍተኛ ተስፋ መቁረጡ ውስጥ የገባው በዘረኝነትና በዝርፊያ የተገነባው የእነ መለስ ሰፈር ይይዘው ይጨብጠው አጥቶ ከአሜሪካ መንግስት ጋር ግንኙነቴን ሊያሻሽልልኝ የሚችል አምባሳደር ባገኝ ከሚል ቀቢጸ ተስፋ ከወለደው ጭንቀት ሰው ማፈላለጉን እንደተያያዘው ተገልጿል።

ወያኔ ሌላ አምባሳደር ቢሾምም ከኦባማ አስተዳደር ጋር የመታረቅ እድሉ የመነመነ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል ያሉት ታዛቢዎች፣ የጉልቻ መለዋወጡ ምንም ልዩነት እንደማአመጣም ተናግረዋል:: የኦባማ አስተዳደር ጸቡ ከዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዘናዊ ጋር እንጂ ከዶ/ር ሳሙኤል ጋር ባለመሆኑ፣ አዲሱ ተሿሚም ለወያኔ የሚፈይደው አንዳችም ነገር የለም ሲሉ አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

አይጋ ፎረም የተባለው የመለስ ዜናዊ አፈ ቀላጤ ድህረ ገጽ የኦባማ አስተዳደር በሀገራችን አፓርታይድ መሰል አገዛዝ የዘረጋውን ወያኔን ማግለሉ፡ ከፍተኛ ብስጭት ፈጥሮበት ፕሬዚዳንት ኦባማን በቆዳ ቀለማቸው አንኳሶ በመጥራት እነሱ ቢያገሉን እኛ ምን ቸገረን የሚል በወያኔያዊ ዘረኝነትና እብሪት የተቃኘ ጽሁፍ አውጥቶ እንደነበርና በተለያየ የዓለማችን ክፍሎች ተበትኖ የሚኖረውን ኢትይጵያዊ ማስቆጣቱ ይታወቃል።

## ኢትዮጵያ እውቀቱ በሌላቸውና ጤና . . . ከገጽ 1 የዞረ

ባካባቢው ያለው የኦሮሞ ህዝብ የወያኔን አገዛዝ እንደማይቀበል የገለጸችው ተማሪ ሊናኒ ፣ በአጭር ጊዜ ቆይታዋ የተረዳችው ነገር ቢኖር በኢትዮጵያ ወስጥ ያለው አገዛዝ ስልጣኑን ለማቆየት ምንም አይነት ሀይል ከመጠቀም ወደ ሁዋላ የማይል የዘቀጠ አገዛዝ መሆኑን ነው ብላለች።

አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ሲናገሩ ተማሪዋ በኢትዮጵያ ወስጥ ያለውን የዘር ፖለቲካ በአጭር ጊዜ ተረድታ ይፋ ማድረጓ፣ በአገሪቱ ውስጥ በስውር ሲደረግ የነበረው የዘር ፖለቲካ ለውጭ አገር ሰዎች እንኳ ሳይቀር በግልጽ የሚታይ እየሆነ መምጣቱን ያሳያል ብለዋል።

እነዚህ ሰዎች አክለውም ምናልባት ወዶ ዘማቾቹ ወደ ትግራይ ክልል ቢሄዱ ኖሮ ልዩ አቀባበል ተደርጎላቸው በክብር ይሸኙ ነበር ካሉ በሁዋላ፣ማንኛውም የውጭ ዜጋ ከትግራይ ክልል ውጭ የሚያደርገው ጉዞ በወያኔ ሰላዮች ክትትል እንደሚደረግበትና በአገዛዙ ሰዎችም እንደማይወደድ ታውቋል።

አንዳንድ ባለሀብቶች እንደጠቆሙን ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ የሚሄዱ ባለሀብቶች ሳይቀር በትግራይ ክልል ውስጥ ኢንቨስት ካላደረጋችሁ ወይም በሌሎች ክልልሎች ኢንቨስት ካደረጋችሁ በትግራይ ክልል አንድ ትምህርት ቤት ወይም የጤና ኬላ መስራት አለባችሁ እንደሚባሉ ተናግረዋል። ብዙ ባለሀብቶችም ቦታዎችንና የገንዘብ ብድር የሚያገኙት ለትግራይ ክልል ለመስራት ቃል በገቡት ፕሮጀክት መጠን ነው ተብሏል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## ኢትዮጵያ ዛሬም የብሔረሰቦች እስር ቤት ናት!

ግንቦት 7 በደንቨር በጠራው ስብሰባ ላይ **በኤፍሬም ማደቦ** የቀረበ **ክፍል 3** (የመጨረሻ ክፍል)

ጠላታችን አንድ ነዉ፤ችግራችን ተመሳሳይ ነዉ የምንኖረዉ አንድ አገር ዉስጥ ነዉ፤ አንዳንዶቻችን የቆምነዉ ለራሳችን ብሔረሰብ ነፃነት ነዉ፤ አንዳንዶቻችን ደግሞ ትግላችን ህብረ-ብሔር ነዉ ፤ አንዱ ብሔረሰብ የሚኖረዉ በሌላዉ ብሔረሰብ Context ዉስጥ ነዉና ሲዳማዉ ነፃ ሳይወጣ ወላይታዉ ነፃ ነኝ ማለት አይችልም፤ ኦሮሞ በሚረገጥበት አገር አማራዉ እፎይ ብሎ በሠላምና በነፃነት መኖር አይችልም። ስለዚህ የግል ጉዞአችንን ትተን አንድ ላይ እንሁንና ሁላችንንም ከወያኔ ዘረኝነትና እርግጫ ነፃ እናዉጣ።

የመጨረሻዉ መጀመሪያ እንደተጀመረ በዉል የተረዳዉ ወያኔ ሁለት ነገሮችን የትግራይ ህዝብ እንዲያዉቅለትና አዉቆም በተጠንቀቅ እንዲቆምለት ይፈልጋል።

**አንደኛ**:- ከትንሽ እስከ ትልቅ ከደሃ እስከ ኃብታም ሁሉም የትግራይ ህዝብ በወያኔ ስርአት ተጠቃሚ እንደሆነ ማሳወቅ ይፈልጋል፡፡

**ሁለተኛ**:- የትግራይ ህዝብ ዕድገትና ብልፅግና ወይም በጥቅሉ የትግራይ ህዝብ ህልዉና ከወያኔ ህልዉና ጋር በቀጥታ የተያያዘ መሆኑንና ወያኔ ከጠፋ የትግራይ ህዝብ የመኖር ዋስትና አብሮት እንደሚጠፋ ማሳወቅ ይፈልጋል።

ወያኔ ሥልጣን እንደያዝኩ እቆያለሁ ብሎ የሚተማመነዉ ህዝብን ከህዝብ ጋር በማጋጨት ነዉና ይህንን የትግራይ ህዝብ እንዲያዉቅለት የሚፈልገዉን የዉሸት ስብከት የተቀረዉ የኢትዮጵያ ህዝብም እንዲያዉቀዉ ይፈልጋል። እዚህ ላይ አንድ ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር ወያኔ ትናንት የመጣ ጉድ ነዉ! የትግራይ ህዝብ ግን ከንጉስ ኤዛና በፊትም ሆነ በኋላ ዛሬ፤ ነገና ለዘላለም የነበረ፤ ያለና የሚኖር ኩሩና ጀግና የኢትዮጵያዊ ህዝብ አካል ነዉ።

ወገኖቼ ዛሬ የአገራችንን ደህንነት አደጋ ላይ ወድቋል፡የዚህ ምክንያት ደግሞ አንዱ እየዘረፈ ጠግቦ የሚበላ ሌላዉ ደሞ በዘረኝነት ሰንሰለት ታስሮ የበይ ተመልካች መሆኑ ነዉ፡ ከበራፉ ላይ ሞፈር ተቆርጦ እሱ እየደኸየ የሌሎች እርሻ ሲለማ መመልከት የሚፈልግ ሰብዓዊ ፍጡር የለም፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ከፍተኛ የጥሬ ኃብት ክምችት በሚገኝባቸዉ አካባቢዎች የሚኖረዉ ህዝብ ይህንን የኃብት ክምችት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ መጠቀም ካልቻለ ዛሬ ናይጄሪያ ናይል ዴልታ ዉስጥ የሚታየዉ ችግር ነገ የኛም አገር ችግር ሊሆን ይችላል፤ ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ወያኔ የተያያዘዉን ስግግብግብ የንብረት ዝርፊያ ለማስቆም ቆርጦ መታገል አለበት፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ሥልጣን ላይ የወጣ ቡድን የራሱን ዘር፤ጎሳ ወይም የመጣበትን አካባቢ ብቻ እየጠቀመ የሚገዛገበት ዘመን ማክተም አለበት፡፡

የዘር መድልዎን ለማጥፋት የሚደረገዉ ትግል አስፈላጊ ወዳልሆነ ጽንፍ እንዳይወስደንና ጠባሳዉ የማይሽር መጥፎ ትዝታ ጥሎብን እንዳያልፍ የዘር መድልዎው ተጠቃሚ የሆኑ ወገኖች የአገዛዙን ዘረኝነትና ኢሰብአዊነት ተቃውመው በስማችን ይህ ግፍ ሲፈጸም ዝም ብለን አናይም ማለት ይገባቸዋል፡፡

ዛሬ እኛ ኢትዮጵያዉያን መተንፈስና መታገል አንድ የሆኑበት ግዜ ላይ ደርሰናል፡: ከሁለት አንዱን ያቆምን ለታ መሞታችን አይቀርም፤ ወገኖቼ መተንፈስ ስናቆም የምንሞተዉ እኛ ነን፤ መታገል ስናቆም ግን እኛም ኢትዮጵያችንም ሁለታችንም እንሞታለን! ኢትዮጵያዊ ሆኖ በአንድ ወቅት ህይወቴን ለአገሬ እሰጣለሁ ብሎ ያልማለ የለም ፤ አገራችን ያንን መኃላ ከኛ የምትፈልገዉ ዛሬ ነዉ፤ ህይወቱን ለአገሩ ለመስጠት የቆረጠ ሰዉ ሌላ የሚከለክለዉ ምንም ነገር የለምና እስኪ ዛሬ እዉቀት ያለን በእዉቀታችን፤ ጉልበት ያለን በጉልበታችን ገንዘብ ያለን ደግሞ በገንዘባችን አገራችን ኢትዮጵያን አለሁልሽ እንበላት።

ወገኖቼ ኢትዮጵያን ማዳን ከአባቶቻችን የተረከብነዉና እኛም ለልጅ ልጆቻችን የምናስተላልፈዉ ኢትዮጵያዊ አደራ ነዉ እንጂ ከድል በኋላ የሚያስሸልመን ዉለታ አይደለም። ለብዙዎቻችን ይህ የምናካሄደዉ ትግል ያቺ ደሃ አገራችን ከዋለችልን ዉለታ አንፃር ሲታይ እጅግ በጣም ትንሽ ነዉ። እንደኔ እንደኔ ይህ ትዉልድ ማሰብ ያለበት አዲስ አበባ ዉስጥ ቦሌና ፒያሳ ማኪያቶ የለመድን ማኪያቶዎቻችንን እየጠጣን እንደኔ አይነቱ አዋሳ ገበያ ዉስጥ ቦርዴ እየጠጣ ያደገዉ ደግሞ ቦርዴያችንን እየጨለጥን ሁለተኛዉንና ትልቁን አገር የመገንባት ትግላችንን እንዴት እንደምንጀምር ነዉ። ለዚህ ነዉ ግንቦት 7 ወሬ አብቅቷልና ባጭር ታጥቃችሁ ለረጂሙ ትግል ተሰናዱ የሚለዉ።

ይህ ትዉልድ ይህንን አገራችንን ያስጨነቃትን አስቀያሚ ስርአት አስወግዶ የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ግምባታ የሚጀምር ትዉልድ ነዉ።

ይህ ትዉልድ ከሱ ቀደም እንደነበረዉ ትዉልድ እርስ በርሱ የሚናቀር ሳይሆን የሚግባባና የሚረዳዳ ትዉልድ ነዉ!፡፡

ይህ ትዉልድ "ዝምበል" አታዉቅም ሳይሆን "ምን አልከኝ" ምን ልታዘዝ የሚል ትዉልድ ነዉ!፡፡

ይህ ትዉልድ የሚያወራ ሳይሆን እየተወያየ የሚሠራ ትዉልድ ነዉ።

ይህ ትዉልድ ወያኔ በ18 አመት መርዙ ያደበዘዘዉን የኢትዮጵያዊነት መንፈስ እንደገና እንዲየቆጠቁጥ የሚያድደርግ የተሀድሶ ትዉልድ ነዉ!፡፡

የዚህ ወጣት ትዉልድ አላማና ፍላጎት የታገለለት ህዝብ እፎይ ሲል መስማት ነዉ እንጂ እንደ ስብሀት ነጋ ጉና አክሲዮንን ፤ እንደ በረከት ስምኦን አምባሰልን፤ እንደ ግርማ ብሩ ዲንሾ ትራንስፖርትን ለመክፈትና የታገለለትን ህዝብ ደም ለመምጠጥ አይደለም። ለወጣቶች አንድ የማሳስበዉ ነገር አለ ፤ የግንቦት 7 ንቅናቄ የናንተ ንቅናቄ ነዉ፤ ግንቦት 7 ወጣቱን ትዉልድ የሚመለከተዉ ይህንን ትግል መርቶ ወደ ተፈለገዉ ግብ ማድረስ እንደሚችል ኃይል ነዉ እንጂ በአንድ ወቅት ብቻ ጥቅም ላይ ዉሎ እንደሚጣል የፕሮጀክት እቃ አይደለም። ለዚህ በቂ ማስረጃ ከፈለጋችሁ ደግሞ 44% የግንቦት ሰባት አመራር አባላት ወጣቶች ሲሆኑ በከፍተኛ አመራሩና ታች ባሉ አባለት መካከል ያለዉን ትልቁን የቀን ከቀን operational ሥራ በአብዛኛዉ የሚሰራዉ የወጣቱ ትዉልድ ነዉ። ወጣትን አስመልክቶ አንድ የፈረንጆች አባባል አለ- ጋዜጦች የሚጽፉትን ሲያጡ አይናቸዉ የሚያርፈዉ ወጣቱ ላይ ነዉ ይባላል- ወጣቱ ትልቅ ነገር እያሰበ ከሆነ ያ' ትልቅ ዜና ይሆናቸዋል- ወጣቱ ስራ ፈትቶ ቁጭ ብሎ ከሆነ ያም ትልቅ ዜና ነዉ!።

ወገኖቼ ዛሬ ብናዉቀዉም ባናዉቀዉም ሁላችንም ለዘረኝነት በሽታ ተጋልጠናል- አንዳንዶቻችን መጋለጣችን አልገባንም፤ አንዳንዶቻችን በዘረኝነት ተጠቅመናል፤ አንዳንዶቻችን ደግሞ የዘረኝነት አደጋ ገብቶን ልናጠፋዉ እየታገልን ነዉ። ዛሬ በዘረኝነት ተጠቃሚ የሆነዉም ሆነ ዘረኝነትን የሚዋጋዉ ሁሉም አገሬን እወዳለሁ ይላል- ወገኖቼ ኢትየጵያንና ኢትየጵያዉያንን የሚወድ ዘረኝነትን ይዋጋል እንጂ ከዘረኞች ጋር ማዕድ አይጋራም! ትናንት የታገልነዉ ለዲሞክራሲና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነበር፤ የዛሬዉ ትግላችን ዘረኝነት ተጨምሮበታል፡: ወንድሞቼና እህቶቼ በአገራችን ጉዳዮች ላይ የምናደርገዉ ተሳትፎ ዛሬ በሚታየዉ መልኩ ከቀጠለ ነገ እንኳን ዲሞክራሲ የምንገነባበት ሲናፍቀን ሄደን የምንጎበኘዉ ወይም ስንሞት የምንቀበርበት አገር አይኖረንም!

ዘረኛዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአንድ በኩል የአገራችን ደህንነት በምስራቁ ድንበራችን በኩል ከፍተኛ አደጋ ላይ እንደሆነ ይነግረናል፡: በሌላ በኩል ደግሞ 80% የሚሆነዉን የአገሪቱ የመከላከያ በጀት የሚልከዉ ወደ ትግራይ ክልል ነዉ። የመለስ ዜናዊና በዶላር ክምችት የሰከሩ ጓደኞቹን የተደበቀ የወደፊት አላማ በዉል ባልረዳም ይህ የአገሪቱን የምድርና የአየር ላይ የዉግያ ችሎታና ብቃት ከመኃል አገር እያነሱ ወደ ትግራይ ክልል የመዉሰዱ ዘመቻ እጅግ በጣም ሊያሳስበን ይገባል። ባጠቃላይ ዛሬ ተወልደን ያደግንባትን ኢትየጵያን ከመበታተን ለማዳን ያለን ተስፋ አንድ ብቻ ነዉ፡፡ እሱም ይህንን ከአባቶቻችን የወረስነዉንና ከዉስጣችን ተሟጥጦ ሊያልቅ አንድ ሀሙስ የቀረዉን የአልገዛም ባይነት መንፈስ አድሰን፤ አብረዉ ሊያስኬዱን የሚችሉ ልዩነቶቻችንን ለበኋላ አስቀምጠን፤ ኃይላችንን፤ እዉቀታችንንና፤ ድርጅታዊ ብቃታችንን አስተባብረን የኢትዮጵያን በትረ ሥልጣን ከፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ላይ ቀምተን ለብቸኛ ባለቤቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማስረከብ አለብን።ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆነ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያን አገሬ የማለት ይቺን አገር በነፃነት ያስረከቡንን ጀግኖች ደግሞ-"ጀግኖች አባቶቻችን" ብሎ የመጥራት መብቱም ሆነ የሞራል ብቃቱ የለዉም!፡፡ አባቶቻችን እየዘለሉ ሄደዉ ደማቸዉን አፍስሰዉ ላቆዩልን አገር እኛ ገንዘባችንንና ትርፍ ግዜያችንን ለመስጠት ጧትና ማታ ባትሪዉ እንደተሟጠጠ መኪና የሚገፉን ሰዉ ሊያስፈልገን አይገባም።

ዴኒቨሮች አንድ የመጨረሻ ነገር ልበልና በጉጉት ወደምትጠብቁት ዉይይት ልዉሰዳችሁ! እኛን የመሰለ ዘመናትን አቋርጦ የመጣ አኩሪ ታሪክ ያለዉ ህዝብ-- ኢትዮጵያን የመሰለ አገርና ኢትዮጵያዊነትን ለጥቂት ዘረኞችና በልተዉ ለመኖር ብቻ ወደዚህ ዓለም ለመጡ የሂሊና ድሀዎች በምንም አይነት አይተዉም። በአለም ላይ ብዙ ሰዉ የሚፈራዉ ነገር ቢኖር ሞት ነዉ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የሚፈራዉ ሞትን ሳይሆን ዛሬ የሚኖረዉን ኑሮና ነገ ምን እሆናለሁ የሚለዉን መልሱ የማይታወቅ ጥያቄ ነዉ። ከዚህ የጨለማ ኑሮ ለምን አልገላገልም እያለ እራሱን የማያጠፋዉ ለዚህ በሞትና በህይወት መካከል ለተንጠለጠለ ኑሮ የዳረጉትን ዘረኞች ማጥፋት የሚችሉ ልጆች አሉኝ ብሎ ስለሚያምን ብቻ ነዉ!፡፡ ያ' እምነት የተጣለበት ልጅ አንቺ ነሽ፡ አንተ ነህ፤ እናንተ ናችሁ እኛ ነን። የኢትዮጵያን ህዝብ ከሚኖርበት አዘቀት ዉስጥ ዛሬዉኑ ማዉጣት አንችል ይሆናል ፤ እኔ ምንም አልጠራጠርም ይህ ህዝብ ነገ ምን እሆናለሁ ብሎ ለሚጠይቀዉ ጥያቄ ግን ትክክለኛ መልስ አለን። ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ከአመታት በፊት ከመቃብር ዉስጥ መይሳዉ ቴዎድሮስን አናዝዞ "ቃልኮ የእምነት ዕዳ ነዉ" እንዳሰኘዉ ቴአትሩን የመመልከት ዕድል የገጠማችሁ ትዝ ይላችኃል ብዬ እገምታለሁ። ወዳጆቼ ዛሬ ለኛ ቃል የእምነት ዕዳ ብቻ አይደለም። **ቃል**- ለሚቀጥለዉ ትዉልድ የምናስተላልፈዉ ኢትዮጵያዊ አደራም ነዉ። ስለዚህ ዛሬ የከፋፋዮችን ሴራ አክሽፈን ፤ የዘረኞችን አጥር ጥሰን ፤ ወያኔ ዘረጋዉን የጎሳ መረብ በጣጥሰን ተቃቅፈን ተደጋግፈን አንድ ላይ እንሁንና የዚህን ጀግና ህዝብ መከራ በቃ እንበል! ንግግሬ ላይ አልፎ አልፎ ለወጣቶች ትኩረት ሰጥቼ ነበር፤ አሁንም ንግግሬን የምዘጋዉ ለዚሁ ለወጣቱ ትዉልድ በማስተላልፈዉ መልዕክት ነዉ።

### ስሚኝ ኢትዮጵአዊት ስማኝ ኢትዮጵያዊ፤

እንደ እባብ ቆዳ ጀርባህ የሚላጥ፤
እንደ ላም ወተት ወዝህ የሚናጥ፤
እንደ ብርቱኳን ልጠዉ ግጠዉ፤
ወዝ ላአብህን መጥጠዉ፤
ይዉጡህል አላምጠዉ፤
ለዉጥ ብለዉ መጥተዉ፤
በየአስሩ አመት ተለዋዉጠዉ።
ምን እንዳይቀር በቃህ ተነስ፤
ምን እንዳይቀር በቃሽ ተነሽ፤
እስር አለ ታሰሩ፡ ሞትም አለ ሙቱ፤
ከሃዲስ ይሞት የለ ክህደት ሞልቶ ባንደበቱ፤
የእዉነት ሞት ህይወት ነዉ እስኪ ለህይወት ሙቱ

**እግዚአብሔር አምላካችን ኢትዮጵያን ይበርክ!**

## የሙስሊሙ ማህበረሰብ የሮመዳንን ጾም በሚጾምበት ጊዜ በሀይማኖት ስም ግጭት ለመቀስቀስ የሚኳትኑ ሀይሎችን ማጋለጥና መፋለም እንዳለበት ግንቦት 7 ገለጸ

ባለፈው አርብ ነሃሴ 15 የተጀመረውን የረመዳንን ታላቅ ጾም በማስመልከት ፣ ግንቦት7 በላከው ደብዳቤ "የሙስሊሙ ማህበረሰብ ለዘመናት ተፈቃቅሮና ተከባብሮ ከኖረው ክርስቲያን ወንድምና እህቶቹ ጋር ሊያጋጩት የሚሞክሩትን የወያኔ ተስፋ ቢስ ሀይሎች ሊፋለማቸው" ይገባል ብላል። ንቅናቄው ለመላው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ባስተላለፈው የመልካም ምኞት መልእክት ላይ ፣ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ባምባገነኖች የሚደርስባቸውን ወከባና እንግልት ተቋቁመው ለዚህ ቀን በመብቃታቸው የተሰማውን ደስታ ገልጿል። "ይሁን እንጂ" ይላል ግንቦት7 "አገራችን ከዘረፊዎችና በሀይማኖት ስም ህዝቡን ለማጋጨት ሌት ተቀን ከሚሰሩ የወያኔ ተስፋ ቢስ ሀይሎች ነጻ ሳትወጣ፤ ጾምንም ሆነ ሌሎች ሀይማኖታዊ ስርአቶችን በሙሉ ልብና ጽሞና ማድረግ አይቻልም።"

ሁሉም የእምነቱ ተከታዮች እምነታቸውን በነጻነት ማራመድ የሚችሉት አገር ስትኖር ነው ያለው ግንቦት 7 ፣ አገራችንን በማፈራረስ ላይ ያለውን የብል አገዛዝ ካለስወገድን በስተቀር ምንግዜም ዘርግተን ከአምላካችን የምንገናኝበት ቁራጭ መሬት እንኳን አናገኝም ብሏል።

በተያያዘ ዜና በቅርቡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ እየተፈጸመ ያለው አንድን ዘር የማጥቃት ዘመቻ ሊቆም እንሚገባው አሳስቧል። የወያኔ እጅ በእምነት ተቋማት ሳይቀር ዘልቆ በመግባት ህዝቡን እያበጣበጠ መገኘቱን የገለጸው ንቅናቄ፤ ድርጊቱ በአፋጣኝ ካልተገታም ወደር የማይገኝለት ጥፋት ሊደርስ እንደሚችል አሳስቧል።

## ፋሽሽቱ መለስ ዜናዊ ቀዶ ጥገና . . . ከገጽ 1 የዞረ

ሲንቀሳቀሱ እንደነበር መመልከቱን ተናግሮአል። በሰለጠነው የቤልጅየም አሰራር እንኳን በአገራቸው ህዝብ መከራና ሲቃይ የተመቻቸ ኑሮ ለሚኖሩ አንደ መለስ ዘናዊ ዓይነት ላሉ ነፍሰ በላ የአፍርካ አምባገነኖች ቀርቶ፤ በህዝብ ለተመረጠ የአገራቸው ጠቅላይ ሚንስቴር በህመም ወቅት በሆስፒተል ጥበቃ የመመደብ ባህል ስለሌለ መለስ ዜናዊን ይጠብቁ የነበሩት የደህንነት ሰራተኞች ከግል ኩባንያ ተቀጥረው የመጡ እንደነበር የማያጠያይቅ ነው ያለው ዘጋቢያችን ለዚህ ስራ ምን ያክል የህዝብ ገንዘብ ውጭ እንደተደረገ ለማወቅ ያደረገው ጥረት ሳይሳካ መቅረቱን አያይዞ ገልጾአል።

ዘጋቢያችን የሆስፒታሉን ሰራተኞች በማነጋገር በቂ መረጃ ለማግኘት አድርጎት የነበረው ጥረት "የበሽተኞቻችንን ሚስጥር ከባለበቱ ፈቃድ ውጭ መስጠት ሙያዊ አይደለም" በሚል ምክንያት ሳይሳካ እንደቀረም ታውቋአል።

የወያኔ ቁንጮዎች ሚያዚያ 26 የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ አከሸፍን ካሉ ጊዜ ወዲህ አስከዛሬ ምንነቱ በትክክል ለህዝብ ባልተገለጹ የተለያየ የህመም ምልክቶች አንድ ባንድ ለህክምና ወደተለያዩ የአለም ክፍሎች እየተመላለሱ እንደሆነ የግንቦት 7 ምንጮች ገልጸዋል ። መለስ ዜናዊ በአ'ዕምሮ ዕጢ በሽታ እንደሚሰቃይ የሚነገር ሲሆን ከዚሁ በሽታ ጋር በተያያዘ ለረጅም ጊዜ ወደብራስልስ ሲመላለስ እንደነበር ይታወቃል ። ሆኖም አሁን በወያኔ አስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ሲቃይ በመቀበል ላይ ያሉ አነ ጀነራል ተፈራ ማሞ በመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ከተከሰሱ ወዲህ ለህክምና ወደ ብራስልስ ሲሄድ የመጀመሪያው እንደሆነ ተያይዞ የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

በተያያዘ ዜና የመለስ ዜናዊ ህመም እንደተሰማ እጅግ አስገራሚ አስተያየቶች ሲሰጡ እንደነበር ለማወቅ ችለናል። አብዛኞቹ አስተያየቶች "በኢትዮጵያ የፈሰሰው የንጹሀን ደም መፍረድ ጀመረ" ሲሉ ሌሎች ደግሞ መለስ ዜናዊ " ከእግዜአብሄር ፊት ለፍርድ ከመቅረቡ በፊት በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሳናየው እንዳይሞት" ጸሎታችን ነው የሚል ይገኝበታል ።

መለስ ዜናዊ በየትኛው የአካል ክፍሉ ቀዶ ህክምና ተደርጎለት እንደተመለሰ ለጊዜው የታወቀ ነገር ባይኖርም ሆስፒታል አስከገባበት ዕለት ድረስ የምግብ ፍላጎቱ በመሞቱ የተነሳ ፈሳሽ ንጥረ ነገር (ግሉኮስ) በመርፌ ይሰጠው እንደነበር ምንጮቻችን ተናግረዋል ።

## በአለም የመጨረሻዋ ደሀ አገር ኢትዮጵያ. . . ከገጽ 1 የዞረ

በሻሸመኔ አካባቢ በግብርና የሚተዳደሩ ገበሬ "ምንም እንኳን አነስተኛ ቢሆንም የምግብ ክምችት አለ።አብዛኛው የእርዳታ እህል የሚሰጠው ግን ለወያኔ ካድሬዎች ነው።" ሲሉ ወያኔ በተደጋጋሚ የሚሰራውን አሳፋሪ እና ኢሰብአዊ ተግባር አስታውሰዋል።

የሚልሱት እና የሚቀምሱት አጥተው በሞት ተርታ ለተሰለፉ ህጻናት የምግብ እርዳታ ለማድረስ የፖለቲካ አቋምን እንደመስፈረት የሚጠቀመው ወያኔ የእርዳታ እህልን እንደ ፖለቲካ ድጋፍ ማግኛ እና ትርፍ ማጋበሻ እንደሚጠቀምበት የታወቀ ነው።

የኦሮሚያ ምክትል ፕሬዝዳንት የሚል የይስሙላ ስልጣን ያለው አብዱልአዚዝ መሀመድ "ወያኔ ለካድሬዎቹ ብቻ የምግብ እርዳታ አያደርግም፤ ሰዎች እየተራቡ እያየን ዝም አንልም ብሎ"፤ በረሀብ እንዲያልቁ በተፈረደባቸው የኦሮሞ ገበሬዎች ላይ አላግጧል።ወያኔ የኦሮሞን ህዝብ አዋርዶ እና አንገት አስደፍቶ ለመግዛት እንደመሳሪያ ከሚጠቀምባቸው ተላላኪዎች አንዱ የሆነው አብዱልአዚዝ አለቆቹን ለማስደሰት የሰጠው መልስ እሱን ከመሰሉ ሆድ አደሮች የሚጠበቅ ነው ተብሎአል።

## ወያኔ ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁንን . . . ከገጽ 1 የዞረ

በፖለቲካ አምነታቸው ምክንያት መታሰራቸውን የአለማቀፍ ድርጅቶችና ዲፕሎማቶች እንደሚስማሙበት የገለጸው መጽሄቱ፤ የቴዲ አፍሮ መፈታት በወይዘሪት ብርቱካን አላግባብ መታሰር ላይ የሚነሳውን ተቃውሞ ሊያባብሰው ይችላል የሚል ፍርሀት በወያኔዎች ዘንድ ማደሩን መጽሄቱ ዘግቧል።

በተያያዘ ዜናም እንደሌባ ሾልከው በመግባትና በመውጣት የሚታወቁት የወያኔ ሹመኞች፤ ሰሞኑን በእንግሊዝ አገር ተገኝተው በጣም ለሚቆጠሩ የህወሀት አባላት መግለጫ ሰጥተዋል። በአማራ ህዝብ ስም የሚነግደውና መላ አእምሮውን ለወያኔ ሹመኞች አሳልፎ የሰጠው የስም ምክትል ጠ/ሚኒስትር አዲሱ ለገሰ፤ በእንግሊዝ አገር ተደብቆ በመግባት ባደረገው ስብሰባ የተገኙት የክልልሉ ተወላጆች ሳይሆኑ የትግራይ ተወላጅ የህወሀት አባላት ናቸው። አዲሱ ወደ እንግሊዝ የተጓዘው እንደባልደረቦቹ አባይ ጸሀዬ ፓውንድ ለመመንዘር አለመሆኑን የተናገሩት አስተያየት ሰጪዎች፤ የግለሰቡ ተልእኮ በአማራው ህዝብ ላይ በተለይም ከእነ ጄኔራል ተፈራ ማሞ እስር ጋር በተያያዘ እየተነሳ የመጣውን ተቃውሞ ለማብረድ ነው።

እነ ጀነራል ተፈራ ማሞ የህወሀት ወሮበሎችና እንደነ አዲሱ ለገሰ ያሉ ባንዳዎች የሚያደርጉትን አገር የማፈራረስ ስራ በመቃወማቸው በግፍ ለእስር መዳረጋቸው የሚታወቅ ሲሆን፤ የመኮንኖቹ መታሰርም በብአዴን ውስጥ ትልቅ ትርምስ መፍጠሩ ይታወሳል።

## በኢትዮጵያ ሰላማዊ ፖለቲካ ትግል . . . ከገጽ 1 የዞረ

አንድነት በመግለጫው ባለፈው እሁድ በአዳማ ጠርቶት የነበረው ህዝባዊ ስብሰባ ወያኔ ስብሰባዎችን ለማወክ እና የተቃዋሚ መሪዎችን ለማዋረድ ሆን ብሎ ባሰለጠናቸው ዱርዬዎች የተመራ መሆኑን ጠቅሶ "በነጻ የመሰብሰብና ሀሳብን በነጻ የመግለጽ ህገመንግስታዊ መብት በህገ ወጥ መንገድ እና በውንብድና ድርጊት ተጣሰ" ከማለቱም በተጨማሪ ይህ በአዳማ የታየው ድርጊት የወያኔ እውነተኛ ባህርይ ያጋለጠ ነው ብሎታል። በተመሳሳይ በስብሰባው ላይ በክብር እንግድነት ተገኝተው ድብደባ የተፈጸመባቸው ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ባወጡት መግለጫ "በአድማ አዳራሽ የተፈጸመው የውንብድና ተግባር በግልጽ የሚያሳየው ነገር ቢኖር ፓርቲዎች በቅድመ ምርጫ ተንቀሳቅሰው አላማቸውን ለማስረዳት፤ ዕጩዎችን ለመመልመልና ህዝብ እዲመርጣቸው ለመንቀሳቀስ ፈጽሞ እንደማይችሉ ነው ካሉ ቦሃላ በግልጽ የትኛው የተቃዋሚ ፓርቲ አንዳለ ሳይገልጹ በደፈናው በአዳማ የተከሰተው ከአሁን ቦሃላ ሰላማዊ ፖለቲካ ትግል በዚህች አገር ለማድረግ አይቻልም ከሚል ድምዳሜ የደረሱትን የፖለቲካ ድርጅቶች አቋም ትክክለኛነትን የሚያረጋግጥ እርምጃ ነው" ብለዋል ።

ግንቦት ሰባት ቀደም ሲል ስለ ወያኔ መሰረታዊ ባህርይ በሰጠው ትንተና «ሰላማዊ ትግል በአገሪቱ ውስጥ ለማካሄድ ቢያንስ መሰረታዊ ለሆኑ የሰው ልጆች የሰብአዊ መብቶች ከበሬታ ያለው እና ስለ ህግ የበላይነት ግንዛቤ ያለው አገዛዝ በስልጣን ላይ መኖሩ የግድ አስፈላጊ ነው፤ ወያኔ ግን ለእንደነዚህ ያሉ እጅግ አነስተኛ ነገር ግን መሰረታዊ ለሆኑ እሴቶች ምንም ደንታ የሌለው ፍጹም ሓላቀር ሀይል ነው በማለት መግለጹ ይታወሳል።አሁን በገሀድ ሁሉም የፓለቲካ ፓርቲዎች እያስተዋሉት የመጡት ወያኔ ለሰላማዊ የፓሊቲካ ትግል የሚመጥን ድርጅታዊ ባህርይ የሌለው ፋሺስታዊ ድርጅት መሆኑን እና በህገሪቱ የህግ የበላይነት ለማስፈን፤ ነጻነት እና ዴሞክራሲን ለመቀዳጀት የሚቻለው በሁለገብ የትግል ስልት የሚታገዝ ወያኔን ጠራርጎ መጣል የሚችል ድርጅታዊ ብቃት በጋራ ማጎልበት ሲቻል ብቻ እንደሆነ የጋራ ግንዛቤ እየተፈጠረ መጥቶአል ተብሎአል።

ግንቦት ሰባት ቀድም ሲል በወያኔ በሚያዘጋጀው መጪው ምርጫ ተብዬ ድራማ ማን ስንት እጩ ማቅረብ እንዳለበት፤ ማን ስንት ወንበር ማሸነፍ እንዳለበት፤ማን መዳኘት እንዳለበት በወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ ቀድሞ የተወሰነ ነገር መሆኑን ተንትኖ በዚህ ምርጫ በሚመስል ተውኔት ተቋዋሚዎች መሳተፋቸው ምንም ሀገራዊ እርባና እንደማይኖረው መግለጹ ይታወሳል።

በሀገር ውስጥ ወያኔን በሰላማዊ ትግል ብቻ መታገል ይቻላል ይሉ የነበሩ አንዳንድ የፓለቲካ ፓርቲዎች እና ታዋቂ ፓለቲከኞች በወያኔ ለከት ያጣ ግፍ እየተገፉና አፈና እየደረሰባቸው የሚከተሉትን የትግል ስልት ምንነት ቁጭ በለው ለመፈተሽ እየተገደዱ መሆናቸውን በጭንቀት ስሜት ሲገልጹ ይህ የመጀመሪያው አንዳልሆነ የፖለቲካ ተንታኞች ይስማሙበታል።

## በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ አገዛዝ በመማረር . . ከገጽ 1 የዞረ

በተያያዘ ዜናም ሰሞኑን አራት አትሌቶች ለውድድር በሄዱበት ስኮትላንድ አገር ውስጥ መጥፋታቸው ተዘግቧል። የ200 ሜትር ሯጭ የሆነችው ቤተልሄም ሸዋ ታጠቅ፤ የሴቶች የ400 ሜትር የመሰናክል ሯጭ ሆነችው ፈለቀች በቀለ፤ የ 400 ሜትር ራጭ የሆነው ሀንስ ታደሰና የ400 ሜትር መሰናክል ሯጭ የሆነችው ትራስ ሀይለስላሴ በእንግሊዝ አገር ጥገኝነት ለመጠየቅ በመዘጋጀት ላይ መሆናቸው ታውቋል። እነዚህ አትሌቶች በቀጥታ በቴሌቪዥን በሚተላለፍ የሩጫ ዝግጅት ላይ ይሳተፋሉ ተብሎ ሲጠበቅ መጥፋታቸው የታወቀ ሲሆን፤ የወያኔው አገዛዝ በዘር ላይ የተመሰረተውን አገዛዙን እስካልቀየረ ድረስ አገራቸውን ጥለው የሚጠፉ አትሌቶች ቁጥር እየጨመረ እንደሚሄድ የተለያዩ አስተያየቶች ያመለክታሉ።


## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

### የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢያችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ያይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org